# ደምብ/ሥርዓት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

| | |
|---|---|
| ተዛማጅ ግብአቶች፡- | ABA, ABA-RC, BBB, CNA, CNA-RB, CND, CNE, DDA-RA, DJA-RA, DJA-RB, ECN, FFA, FFA-RA, IGK-RC, IPD-RA, JFA-RA, KEA-RA, KGA-RA |
| ሃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡- | የት/ቤት ድጋፍ እና መሻሻል<br>Chief Operating Officer |
| ተዛማጅ ምንጮች፡- | Annotated Code of Maryland, Business Regulation Article, § 6-101; Criminal Law Article, § 13-1803, § 13-1813; Montgomery County Code, §30-4(b) |

## ከትምህርት ቤት ጋር ስለተገናኘ የገንዘብ ማሰባሰብ

I. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ወይም በመወከል ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኘ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች የትምህርት ሠዓት ሳይባክን፣ አስተማማኝ የተማሪዎች ደህንነት ጥበቃን ለማጠናከር፣ ለሁሉም ተማሪዎች የጋራ የሆነ ትምህርታዊ ተሞክሮ ድጋፍ ለመስጠት፣ እና ተገቢውን ሃላፊነትን/ተጠያቂነትን ሥርዓት ሒደትን ጭምር ለመዘርጋት

II. ትርጓሜዎች

A. የወላጅ እና የማህበረሰብ ቡድኖች በዚህ የሚገታ ባይሆንም፣ Parent Teacher Associations, Parent Teacher Student Associations, foundations, and booster clubs የመሣሰሉትን ያካትታል።

B. በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረገ ማለት እንደ ት/ቤት ወኪል የሥራ ባልደረባ ተመድቦ የሚደረግ እንቅስቃሴ እና በርእሰመምህር እና/ወይም ከ "Office of School Support and Improvement (OSSI)" በሚመለከተው ተባባሪ ሱፐር ኢንተንደንት አማካይነት የተፈቀደ እንቅስቃሴ ማለት ነው።

III. የቅደም-ተከተል ሥርአቶች

A. ፈቃድ ስለመስጠት-Approval

1. በ MCPS፣ በትምህርት ቤቶች፣ ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው ቡድኖች አማካይነት የሚደረግ የገንዘብ ማሰባሰብ ተግባር የጊዜ ሠሌዳ ከመውጣቱ በፊት፣ ማስታወቂያ ከመነገሩ ወይም ከድርጊቱ አስቀድሞ መፅደቅ አለበት።

   a) ርእሰመምህራን ወይም ተወካዮቻቸው በትምህርት ቤቶቻቸው ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው ቡድኖች አማካይነት የሚከናወን የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎችን የማጽደቅ/የመፍቀድ ሃላፊነት አለባቸው።

   b) በ OSSI የሚመለከተው ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት በበርካታ ትምህርት ቤቶች አማካይነት የሚካሄዱ ወይም በካውንቲ አቀፍ የተማሪዎች ድርጅቶች የሚከናወኑ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎችን ያፀድቃል-ታፀድቃለች።

c) በ MCPS ሠራተኛ ቡድኖች አማካይነት የሚከናወኑ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች በዋና የሥራ ኃላፊ-chief operating officer አማካይነት መጽደቅ አለበት።

2. ትምህርት ቤት የሚያካሄዳቸው ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚያደርጋቸው ቡድኖች የሚያከናውኑት የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ላይ በሙሉ የ MCPS የሥራ ባልደረባ ይኖራል/ትኖራለች።

B. የማስተዋወቂያ ቁሳቁሶች

በትምህርት ቤቶች ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው ቡድኖች አማካይነት የሚዘጋጁ ስለገንዘብ ማሰባሰቢያ የማስተዋወቂያ ቁሳቁሶች የሚከተለው መግለጫ እንዲጻፍባቸው ያስፈልጋል፡- -እነዚህ ቁሳቁሶች ወይም አገልግሎቶች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ፣ ወይም በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ ወይም በትምህርት ቤት አማካይነት ስፖንሰር አልተደረጉም- "These products or services are neither sponsored by nor endorsed by the Montgomery County Board of Education (Board), the superintendent of schools, or this school."

2. የማስተዋወቂያ፣እና የመረጃ ቁሳቁሶች ሥርጭት መከናወን ያለባቸው ከ"Board Policy CNA" መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት።

C. ስለ ተማሪ ተሳትፎ እና ስለ ተማሪ ደህንነት

1. ማንኛውም ተማሪ እንዲያዋጣ-እንድታዋጣ ወይም በገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ ላይ ለመሣተፍ አይገደድም-አትገደድም።

2. ለተማሪ ደህንነት ሲባል፣ በማንኛውም ተማሪ አማካይነት የሚከናወን በመኖሪያ አካባቢ ቤት-ለ-ቤት ወይም መንገድ መሃል በሚደረጉ ሽያጮች የገንዘብ ማሰባሰብን ማካተት የለበትም።

3. ተማሪዎችን የሚያሳትፍ የገንዘብ ማሰባሰብ በሚከናወንበት ጊዜ ከተማሪዎቹ እድሜ ጋር የሚመጥን የአዋቂ/የጎልማሳ ቁጥጥር-ክትትል መደረግ አለበት።

D. የትምህርት ሠዓት ስለመጠቀም

1. ለገንዘብ ማሰባሰብ የሚውል ማናቸውም የትምህርት ሠዓት ከማስተማር ዓላማው ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት።

2. በእነዚህ ድርጅቶች አማካይነት የሚከናወኑ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎችን በሙሉ፣ እና፣ በተለይም፣ የትምህርት ሠዓት መጠቀምን ወይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተፅእኖ የሚፈጥር ከሆነ፣ የየእለት ሽያጮችን መሰብሰብን የወላጅ እና የማህበረሰብ ቡድኖች እቅድ በማድረግ ይቆጣጠራሉ።

E. ግብረሠናይ ድርጅቶች-Charities

ትምህርት ቤቶች ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚያደርጋቸው ቡድኖች ከልግስና ጋር ለተያያዙ ዓላማዎች ገንዘብ ወይም እርዳታዎችን መሰብሰብ ይችላሉ።

1. ስፖንሰር አድራጊ ሠራተኞች የግብረሠናዩ ህጋዊነት እና ታሳቢ የተደረጉ ተጠቃሚዎችን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

2. ይህንን ወይም ሌላ የ MCPS ደምቦችን ወይም የቦርድ መርኖችን የማያሟላ ከሆኑ ርእሰመምህር የትምህርት ቤት ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚያደርግ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ እንዳይካሄድ መከልከል ይችላል-ትችላለች። ለበጎ አድራጎት ዓላማ ገንዘብ ለማሰባሰብ ፈቃድ የመስጠት ወይም የመከልከል ውሳኔ ለመስጠት የበጎአድራጊው ድርጅት አመለካከት ምክንያት መሆን የለበትም።

F. ኃላፊነትና ተጠያቂነት-Accountability

1. በትምህርት ቤቶች ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ ቡድኖች አማካይነት በሚካሄድ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች የተሰበሰበ ገንዘብ በ MCPS የፋይናንስ አጠቃቀም አሠራር ማኔጅ የሚደረግ የትምህርት ቤት የተናጠል አካውንት ውስጥ ገቢ መደረግ ይኖርበታል።

2. ትምህርት ቤቶች እና በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረጉ ቡድኖች ስለ ገንዘብ ማሰባሰብ እና ክፍያ ተገቢውን የሒሳብ መግለጫ-ማስረጃ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

3. የማስተዋወቂያ ቁሳቁሶቹ የገንዘብ ማሰባሰብን እንቅስቃሴ ዓላማ በትክክል መግለጽ አለበት፣ እና ከእንቅስቃሴው የተገኘ ገቢ በጠቅላላ ባሉት መርሆች እና ሥርዓቶች መሠረት ለታሰበላቸው ዓላማ መከፈል ይኖርበታል። ከታቀደለት አላማ በላይ ገንዘብ የሚሰበሰብ ከሆነ፣ ስለሚሰበሰበው ገንዘብ ሁለተኛ ወገን ተጠቃሚ ስም በማስተዋወቂያ ቁሳቁሶቹ ላይ እንዲገለጽ ይመከራል።

G. ከትምህርት ቤት አመራር ጋር ስለመተባበር

ወደ ጋራ ግብ ለመድረስ የተቀናጀ ጥረት ለማድረግ እንዲያመች ትምህርት ቤትን በመወከል ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ የትምህርት ቤት ስብስቦች የገንዘብ ማሰባሰብ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ የወላጅ ወይም የማህበረሰብ ቡድኖች፣ የገንዘብ ማሰባሰቡ ዓላማ ከ"Board Policy CND" ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማረጋገጥ ከርእሰመምህር(ራን) ጋር በቅድሚያ ቅንጅት/ትብብር ማድረግ አለባቸው School-Related Fund-Raising-ከትምህርት ቤት ጋር ስለሚገናኝ የገንዘብ ማሰባሰብእና የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎቹ ከማስተማር ፕሮግራም ወይም ቀደም ሲል የታቀደ በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረግ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ጋር መጣረስ-መጋጨት እንዳይኖር። እንቅስቃሴው ተገቢ አለመሆኑ ሲታወቅ ርእሰመምህሩ(ሯ) ለወላጅ ወይም የማህበረሰብ ቡድን-ቡድኖች አመራር የማሳወቅ ሃላፊነት አለበ(ባ)ት።

H. ስለ እቃዎች ወይም የመገልገያ መሣሪያዎች ግዢ እና የስጦታ እቃዎችን ስለመቀበል

1. ለትምህርት ቤት የተናጠል እንቅስቃሴ ፈንዶች ቁሳቁሶችን እና መገልገያ መሣሪያዎችን ለመግዛት ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ሁሉ በግዢ ክፍል የተዘጋጀውን መመሪያ መከተል ያስፈልጋል።

2. ስለ ስጦታ (የእርዳታ) እቃዎች የመቀበል አፈጻጸም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-"MCPS Regulation DJA-RB" ላይ ተገልጿል፣ ከመደበኛ ባጀት ውጭ የሆነ ፈንድ በመጠቀም ስለሚከናወን የቁሳቁስ እና የእቃ ግዢዎች እና በእርዳታ የሚሰጡ ቁሳቁሶችን ስለመቀበል-Purchases of Materials and Equipment Using Nonappropriated Funds and Acceptance of Donated Items።

3. በቦርድ ፖሊሲ "Board Policy CNE" መሠረት ለካፒታል ማሻሻያዎች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የመንግስት ባጀት ውጭ የተለየ ፈንድ የመቀበል አሠራር መመሪያ ቦርዱ ያዘጋጃል በሞንትጎመሪ ካውንቲ ገቢዎች ባጀት ያልተመደበላቸው የፋሲሊቲ ማሻሻያዎች Facility Improvements That Are Not Funded With Montgomery County Revenues።

I. የመጫወቻ አክቲቪቲዎችን ማከናወን

1. MCPS ን በመወከል እንደ ቢንጎ ወይም ሎተሪ የመሣሰሉ የመጫወቻ እንቅስቃሴዎችን ለማካሄድ የሚያቅዱ የወላጅ ወይም የማህበረሰብ ቡድኖች በሜሪላንድ ህግ ድንጋጌ መሠረት፣ አግባብነት ያለውን ፈቃድ ማግኘት እና በሚታይ ሥፍራ ላይ ማኖር ያስፈልጋል።

   ማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ ቡድኖች እንደ ሎተሪ፣ ወይም ቢንጎ የመሣሰሉ የንግድ ፍቃድ የሚያስፈልጋቸውን የመጫወቻ እንቅስቃሴዎችን አያከናውንም።

**ስለ ደንቡ ታሪክ፦** New Regulation, June 20, 2013; revised December 20, 2013።